# አለማየት

## ሀ. ዐይን

የሁሉም ሰው__ ዐይኑ
ከግንባሩ ስር__ መሆኑ
ቢታወቅም_____ዕውነቱ
ግን የዐይን ልዩነቱ
ዕውር አለማየቱ
መሆኑ ዐይነ ስውር
ሳይሆን የሚያከራክር
የሚያየውን ዐይን ጭምር
እንድንመረምር
ስለ ዐይን ብንሆን ዳኛ
ሽሁራራ ይሁን ቀጥተኛ
እያዩ ማየት__ የሚሳነው
ዕውር አይጠፋም ላስተዋለው።

## ለ. ጨለማ

የጨለማን _ብፅዕና
ጠርዝየለሽ _ መሆኑንና
አሰቦት አልቦ _ወና
ደንበርም _አልቦነቱን
የማየት ችሎታ _ዕጦቱን
አላቂ _አለመሆኑንና
የባህሪያቱን _ ህልውና
ጨለማን _ውስጡ ሆነህ
ወደ ውስጥ _ ተመልክተህ
ዐይኖችህን _ ጨፍንና
ፈትሸው _ በጥሞና።

ጥር 2001

abraham beyenne